□ት ሬ □□ አ ስ ተ □□ ር

# ት ሬ ነ □ ሪ ት □ □ □

# DIRE NEGARIT GAZETA

## OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

| ሁለተኛ ዓመት ቁጥር 12<br>ድሬዳዋ የካቲት 2 ቀን 2002 ዓ.ም. | በትሬ□□ አስተ□□ር<br>ምክር ቤት □ባቂነት □□□ | 2nd Year No. 12<br>DIRE DAWA - 9th February,2010 |
|---|---|---|

## አዋጅ ቁጥር 12/2002

### የድሬዳዋ አስተዳደር የታክስ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ ጊዜያዊ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር የታክስ ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 19/1998 ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 12/1/ /ሀ/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል::

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ አዋጅ «የድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር የታክስ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር12/2002» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. <u>ማሻሻያ</u>

   የድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር የታክስ ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 19/1998 እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

## PROCLAMATION NO 12/2010

### A PROCLAMATION TO AMEND THE DIRE DAWA PROVISONAL ADMINISTRATION TAX AUTHORITY ESTABLISHMENT PROCLMATION

WHERE AS, it is found necessary to amend The Dire Dawa provisional Administration Tax Authority establishment proclamation No. 19/2005;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 12/1/ /a/ of the Dire Dawa Administration Charter proclamation No. 416/1996 , the Dire Dawa Administration council here by proclaimed as follows;

**1. <u>Short title</u>**

This proclamation may be cited as the “Dire Dawa Provisional Administration Tax Authority Establishment /Amendment/ Proclamation No.12/2010”

**2. <u>Amendment</u>**

The Dire Dawa Provisional Administration Tax Authority Establishment Proclamation No. 19/2005 is amended as follows;

1. የአዋጁ አንቀጽ 1 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 1 ተተክቷል፡፡
   «/1/ ይህ አዋጅ «የድሬዳዋ አስተዳደር የገቢዎች ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 19/1998» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡
2. የአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ /2/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /2/ ተተክቷል፡፡
   «/2/ የባለሥልጣኑ ተጠሪነት ለድሬዳዋ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡ »
3. «የአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል፡፡
   /2/ የገቢዎች ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ በከንቲባው አቅራቢነት በአስተ ዳደሩ ካቢኔ ይሾማል፡፡

3. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በድሬ ነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ድሬዳዋ የካቲት 2 ቀን 2002 ዓ.ም.

አደም ፋራህ

የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ

1. Article 1 of the proclamation is deleted and replaced by the following new article 1
   "1" This proclamation may be cited as " The Dire Dawa Administration Revenue Authority Establishment Proclamation No. 19/2005"
2. sub article (2) of Article 3 of the proclamation is deleted and replaced by the following new sub article (2)
   "2" the authority shall be accountable to the Dire Dawa Administration Finance and Economic Development Bureau.
3. sub article (2) of Article 7 of the proclamation is deleted and replaced by the following new sub article (2)
   "2" The General manager of the revenue authority shall be appointed by the cabinet of the administration up on the recommendation of the Mayor.

**3. <u>Effective Date</u>**

This proclamation shall come into force on the date of its publication in the Dire Negarit Gazeta.

**Done at Dire Dawa , this 9th day of February, 2010**

**ADEM FARAH**

**MAYOR OF DIRE DAWA ADMINISTRATION.**